# የተደበቁ እውነቶች በሳውዲ አረቢያ !

# የመከረኞች ሸኘት !

ክፍል 10

ነቢዩ ሲራክ- ከሳውዲ አረቢያ

## ማየት ማመን !

ካጠፋነው እንማር በበጎው እንበረታታበት ዘንድ ያለፈውን ዛሬ ላይ እያነሳሁ በማዘክርበት ቀጣይ መጣጥፌ በሳውዲ የተለያዩ እስር ቤቶች ስቃይ መከራቸውን ስለሚያዩ ወገኖች፤ በቆንስሉ ግቢ በሚገኘው መጠለያ ስለሚገኙ ወገኖችና አልፎ አልፎ በሰሞነኛ ሰበር ወጋወጌ ያየሁ የሰማሁትን በመረጃ እያደገፍኩ ለማቅርብ ሙከራ ማድረጉ ገፍቸበታለሁ፡፡ የወገኖቸን መከራ ተንተርሸ በማቀርበው መጣጥፍ ምስጋና አክብሮት ድጋፋቸውን የሚገልጹልኝ የመኖራቸውን ያህል የተጣለባቸው ሃላፊነት መወጣት ባልቻሉ የመንግስት ሃላፊዎች ላይ የምሰነዝራቸው ሂሶች የሚያንገበግባቸው ጥቂት ወገኖቸ ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ያወግዙኛል፡፡ አይዞህ የሚሉኝ ሌላው ቢቀር መረጃ ማስተላለፌን ቢወዱትም አደጋ እንዳያስከትልብች እኔን ሆነው ያሳስባቸዋ ! ፍርሃታቸው ለደህንነቴ ካላቸው ስጋት የመነጨ እንደሆነ ይገባኛልና ያበረታታኛል፡፡ ጥቂቶች መረጃየን የሚያንገበግባቸው እያነሳን ከምንጥለው የቀይ ባህር ማዕበል ውሃ፤ የአረብ ሃገሩ አሽዋማ በርሃ በልቷቸው ክንብል ብለው የሚቀሩ ወገኖቻቸው ጉዳይ አይታያቸውም. . .በጩካኝ አዘዋዋሪውች የሚደፍሩ በወጡበት የት እንደደረሱ የማይታወቁ ወገኖች ሮሮን በግላጭ መሰማት መንግስትን እንደመቃወም አድርገው ይቆጥሩታል ! ይህ በመሆኑ እንደ ክራሞታቸው ተቃውሚቸው ቢያይልም አልቀበላቸውም ! የሚናገሩት የአቅማቸውን ያህል፤ ህሳቤያቸው የተሰጣቸውንና ታጠቁትን ያህል ነውና በልዩነታችን ባዝንም አልቃዎማቸውም! በእርግጥ የቆንስል ሃላፊዎችን ብጹዕነት የሚያስረግጥ ስራ መሰራቱንም ሆነ በማቀረበው መጣጥፍ የመረጃ ፍልሰት አለ ሲሉ እንዲህ ነው ብለው አይሞግቱኝም፡፡ ብቻ ጣታቸውን ቀስረው ያስቀስሩብኛል ! መንግስት ከአንድ መቶ ሽህ በላይ ዜጎቹን መብት ጥበቃ ያድረግ ብለን ስናሳስብ "ፍየል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ " እንዲሉ የምናስተጋባውን ዋንኛ ሃሳብ ፈንግለው በሃር ቤት ስለሚታየው የተሳለጠ እድገትና ስለ መልካም አስተዳደሩ መስፈን አንደ ባዕድ ባይተዋር ማስረዳቱ ይቀላቸዋል . . .!

በማቀርበው መጣጥፍ ዙሪያ ግራ ሲጋቡ መረጃ የሚጠይቁኝን ሳገኝ ደስታየ ወሰን ያጣል፡፡ ያን ሰሞን አንዲት የፌስ ቡክ Face Book ወዳጀ በቆንስሉ መጠለያ የሚገኙ ወገኖቻችን ታሪክ አንብባ ነበርና ስለሁኔታው በቂ መረጃን እሰጣት ዘንድ ስትጠይቀኝ የተሰማኝ ደስታ ወሰን አልነበረውም፡፡ "እኛ በምንኖርበት ሃገር ይህ ሁሉ አለን ነው የምትለኝ ?" ያለችኝ እህት. . . "ኣዎ!" ነበር መልሴ . . . ይህችን እህቴ በአካል ኣላውቃትም . . . እውነቱን ውሸት ማለት እንደሚቀላቸው ወንድሞቸ አለመሆንዋን በአቀራረብዋ ተረድቻለሁ . . . በክፍል ሰባት መጣጥፌ አንብባ ይህን ጥያቄ ስላቀረበችልኝ ነባራዊውን እውነታ አስረግጦ ለማስረዳት ብቸኛው አማራጭ ያለውን በቦታው ሄዶ ከመረዳት መልካም አጋጣሚ



ሆነልኝ ! ስለሁኔታው ትረዳ ዘንድ ቀጠሮ ያዝን፡፡ በመሰንበቻው አንድ ሌላ ጓደኛዋን አስከትላ በኮሚኒቲው ካፍቴሪያ ተገናኘንና ምሳ ቢጤ እየቀማመስን በጽሁፉ ላይ ስለቀረቡት አንደበቷ ስለተዘጋው እህት፤ ስለ ግመል ጠባቂው ወንድምና ተምር ለቃሚ እህቶች፤ "የምነግርህ አለ. . ." ብላኝ መልዕክት አስቀምጣልኝ በቀናት ልዩነት በቆንስሉ መጠለያ ስደርስ አንደበቷ ተዘግት ስላገኘኋት እህትና በአጠቃላይ ስላቀረብኳቸው የስደተኛ ኢትዮጵያውያን እንግልት ታሪክ ሁሉንም አንስተን መጨዋወት ያዝን ! በተለይ ስለ መከረኛ እህት ለመስማት ጓጉታለች. . .ትንሺ በሁሉም ዙሪያ ካወጋን በኋላ ያች በጸና ታማለች ያልኳት እህት ህመም ጸንቶባት ባንድ ምሽት ነብስ ከስጋዋ በተለየ በሰአታት ልዩነት በድኗ በእራፊ ነጭ አቡጀዴ ተጠቅልሎ ሙሾ ሳይወረድላት በድኗ በማዘጋጃ ቤት ሰራተኞች በጅንባ ጅንቦ በሬሳ መጫኛው መኪና ሲያስገቡት አይቻለሁ. . .ስሜቴን ለመቆጣጠር እየሞከርኩ ሊሰሙት የሚከብደው መርዶው ነገርኳቸው ! እህቶቸ በሃዘን ኩርምት አሉ . . .! ጥቂት እንደመረጋጋት ስንል ጭውውታችን ቀጠልን. . . በውስጥ ደዌ በሺታ ተሰቅዞ አጎንብሶ ይሔድ የነበረውን የግመል እረኛ ወንድም የቆየ የቪዲዮ ምስል አሳይቸ ዛሬ ከህመም ውጋቱ በአንዳንድ ወገኖች ትብብር የመዳኑን መልካም የምስራችና በሰላምና በጤና የተሻለ ስራ እየሰራ መሆኑን በቅርቡ ቆሞ የተነሳውን ፎቶ እያሳየሁ ብነግራቸው በሃዘን የተነካ ስሜታቸውን ማባበል አልተቻለኝም ! እንጀራ ፈልገው

በሚሰደዱ ወገኖቻችን ላይ እየሆነ ያለው እኔ ከምናገረውና ከምጽፈው በላይ ስለመሆኑ ምስክርነት የሰጡኝ እኒህ እህቶችን በማግኘቴ ደስታ ተሰምቶኛል ! "ማየት ለፈለገ ማየት እኮ በእርግጥም ማመን ነው" አልኩ ራሴ ለራሴ !

## እኔና ባይተዋሮች በቆንስሉ መጠለያ . . .

ብዙ ከመናገር ተቆጥቤ ከካፍቴሪያው 300 ሜትር ርቀት በምትገኘው መጠለያ በአሁኑ ሰአት የሚገኙ ታማሚዎችን ለማየት ወደዚያው አመራን፡፡ አንዲት እህት ጥቁር አባያዋን እፊቷ ድረስ ተሸፋፍና የሚለበልበውብ ሃሩር ሳይበግራት ኩርምት ብላ ተቀምጣ ተመለከትናት ፡፡ ታማሚዎችን ጠያቂ መሰለችንና ግር ተጋብተን ሰላምታ ብናቀርብላትም አልመለሰችልንም፡፡ እሷኑ አልፈን በቀጥታ ጸጥታ ወደ ሰፈነባቸው መጠለያ ክፍሎች ጎራ አልን፡፡ አንዲት ጉስቁል ያለች እህት መሬት ላይ ከተነጠፈች ፍራሿ አጠገብ ለልጅዋ ጡጦ እያጠባች አጋጠመን ፡፡ ይህች መጫትና እርጥብ ልጇ በአዲሱ አምባሳደር መርዋን በድሪ ትብብር ልዩ ትኩረት ተደርጎላት ህክምና ማግኘት መጀመሯ ከሁለት ቀናት በፊት መረጃ አግኝቻለሁና ጥሩ ቀን መምጣቱ አስደስቶኛል፡፡ እናም ከሳምንታት በፊት ያየሁዋት ጉስቁል አራስ ተሽሏታል፡፡ ልጇግን ያው ነው . . . እይኑን እያስለመለመ ያችኑ ጡጦ በግድ ላጥባህ ስትለው እንቢ እያላት እናቱ አለማስደሰቱን መረዳት አያዳግትም፡፡"እኔ ደህና ነኝ የልጀ ነገር እንጅ !" ስትል አንገቷን በሃዘኔታ እጥፍ አድርጋና አይኗን በማሙሽ ላይ ተክላ ስትመልስ ሆድ ታባባለች፡፡ ያን ሰሞን የልጇ አለመኖር የምትፈቅድ የነበረችው እናት ዛሬ የእልጇን ትንፋሽ ለማሰንበት ስትታገል ማየቴ ተስፋን ሰጠኝ . . .

አሁን እንዴት ነው ያለሽው ? በደንብ ተሽሎሻል ? ስንል ድንገት ጠየቅናት

"አላህ አምዲላህ ! ይሁን ደህና ነኝ . . . አሁንማ ተሽሎኛል!" አለች አንገቷን ሰበር አድርጋ ጥያቄውን ቀጠልን

መቸነው ከሃኪም ቤት የመጣሽው ? አልኳት

"አሁን. . . ሁለት ቀን ሆነኝ. . . "

"እዚህ ከመጣሽስ ምን ያህል ጊዜ ሆኖሻል ? " አለቻት አንደኛዋ እህት

". . . እኔ ምኑን አውቀዋለሁ እናንተየ ! በየመን አድርጌ ስመጣ አረገዝኩ. . . በጠና ታምሜ ወለድኩ . . .ከዚያ ወዲህ የሆነውን አላውቀውም ! " ስትል አይኖችዋ እንባ አርግዘው ነበር

"ባለቤትሽ ማለት የልጅሽ አባት እዚህ ነው ? ይረዳሻል ?" ሌላኛዋ አከታትላ ጠየቀቻት. . . አላስፈላጊ ጥያቄ ነበርና ሰውነቴን አንዳች ነገር ወረረኝ . . . ". . . እህ. . ." ብላ ትንሽ ከቆዘመች በኋላ ፊትዋን ወደ ልጇ አዙራ ጡጦውን ያስተካከለች አንገቱዋን ደፋ አድርጋ ዝም አለች ፡፡ ዝምታ ነገሰ ! መልስ የለም ! የማይጠየቅ የማይነካ ቦታ መነካቱ ገብቶኛልና ሁኔታውን ለማረጋጋት "በይ አይዞሽ አሁን ተሽሎሻል እየመጣን እንጠይቅሻለን!" በማለት ለማጽናናት ስሞክር ከአጠገቤ የቆሙት እህቶቸ አይናቸው ደም ለብሶ ፊታቸው በሃዘን ድባብ ተውጦ ተመለከትኩ ! ቅጭም ካለፍ ፊታቸው በአይናቸው ላይ የሚገዋለለው ያልፈሰሰ እንባ ልቤ አራደው ! በሩን ለቀን እንደወጣን ፈንቅሎ ሊወጣ የሚታገለውን እንባ ምራቃቸውን እየዋጡ እንዳይወርድ ሌገቱት ቢሞክሩ ያንደኛዋ እህት እንባ እያመለጣት ድምጿን ውጣ ከትላልቅ ቦርሳቸው የሚቻላቸውን ሁሉ አውጥተው ሰጠዋት ዘወር አሉ ! ያችን ክፍል ልቀን ወንዶች ወደሚገኙበት ወደ ሌላኛዋ መጠላያ ክፍል በሁለት እርምጃ ተሻገርን . . ሆዱ ቅጥጥ ብሎ የተነፋው ወንድም አመርና በየመን በርሃ ሲመጣ 45 ያህል ረሳ ቀበርኩ ያለኝን ወንድም የሱፍ በዚያች ክፍል ውስጥ አገኘናቸው. . . አመር በጀርባው ተጋድሞ ጣራ ጣራውን እያየ ያልማል. . . የሚያልመውን እንጃ. . . የሱፍ የደከመ ሰውነቱን ደገፍ አድርጎ የሚንቀሳቀስባትን የእንጨት ምርኩዝ አሽቀንጥሮ አልጣላትም. . ቀን የገፋችለት ምርኩዙን ከጀርባው ትታያለች፡፡ አንድ በጎ አድራጊ ወጣት የካፍቴሪያ ደንበኛ የገዛለትን ጎማ ያለው ዘመናዊ መደገፊያ ምርኩዝ ከፊት ለፊቱ አድርጎ እያሻሻት እሱም አጎንብሶ በሃሳብ ቢጤ የተጠመደ ይመስላል. . . የሆዳችን በሆድ አድርገን ወደ ወንዶቹ ክፍል ሰላምታ አቅርበን ስንገባ ሁሉም ከሄዱበት ነቅተው በተጎሳቆለው ፊታቸው ፈገግታ ነስንሰው ተቀበሉን ! "ወይኔ እነዚህንማ በፎቶ አውቃቸው የለም እንዴ !" አለች የፌ ቡኳ ጓደኛየ እህት ገና እግሯ ከመግባቱ. . . ሳታስበ ደንግጣ ድምጿን መያዝ አቅቷት ! በመጣጥፌ ያየችውን ፎቶ በአይኗ በብሌኑ ማየት ቻለች ! ያየችውን ማመን ቢያቅታት አልፈረድባትም ! ያለችውን አላዳመጡትም. . . ብቻ ወንድሞቸ ጸጥና ረጭ ባለው ቀትር ጠያቂ አግኝተዋልና እየሳቁ ተቀበሉን . . .ምነው ዛሬ ፈገግታው የተለየ ነው ምነው ምን ተገኘ ? . . . አዲስ ነገር አለ ? አልኳቸው መቀመጫ ቢጤ በአይኔ እየፈላለግኩ. . . አመር የአፍ መፍቻ ቋንቋው አማርኛ አይደለምና አማርኛውን የመናገር አቅሙ ውስን ቢሆንም አማርኛ ሲናገር የንግግር ቃናው ኦሮምኛ ተቀላቅሎበት ሊሰሙት ያጓጓል. .

.ለኔ ይገባኛል . . . ኦመር ከተጋደመበት ሊነሳ ሲል ራሱን እያሻሸ ነበር . . . እጁን ፊቱን እያስደገፈ ፈገግ እያለ መናገር ሲጀምር ደግሞ አዲስ ነገር መኖሩ አልጠፋኝም. . . ቀጠለ. . ." . . .ኢባክህ አሁንማ ዲነናል ! ወረከቱ እያለቀ ነው ! በካ ከሰሞኑ ይሄዳሉ ተቡሏል. . .አሁን አንድ ጅዛን በጥይት ተመቶ ሽባ የሆነው ወንድም ወረከት ለማሰራት ቶድሮስ ወስዶታል . . . የሱ ቢቻ ነው የከረ . . . ደሞ ይሄ ሴት ባለልጅ አልሄዲም ብሏል. . . እሱ ብቻ አልሄድም ብሎ አሸግሯል" ሲል ከሚያማምር ጥርሱ የሚነበበው ፈገግታና ደስታ መላ ፊቱ እያስናኘ አገር ቤት የመግቢያ ፈቃድ የማለቅ ተስፋ እንዳለው ብስራት አበሰረን . . . በደስታ ፈነደቅን . . . ለስድስት ወራት ህክምና እንኳ ሳያገኙ በቆንስሉ መጠለያ በወገን እርዳታ እየተደረገላቸው ቢቆዩም አዲሱ አምባሳደር በመጡ ማግስት ህክምና ማግኘት መጀመራቸውና በሁለት ወር ውስጥ ደግሞ ወደ ሃገር ቤት ለመሄድ የይለፍ ወረቀቱ እንዳለቀላቸው የሱፍ እየተከለታተፈ ከምስጋና ጋር አወጋን . . . ዛሬ የደስታ ቀን ነውና ቀልድ ቢጤ ጨማምረን አወጋግተን በሽኝታቸው ቀን እንደምገኝ ቃል ገብቸላቸው ስንወጣ ኦመር እንደ ድሮው ቁጭ ብሎ አልተሰናበተኝም. . . ሆዱም ጎደል ብሎለታል፤ተሽሎታልምና ከተቀመጠበት ብድግ ሲል በነገር ሸንቆጥ አደረግኩት. . . "አይ አንተ ነገር. . ." እየተንከተከተ እጁን በጀርባየ ላይ ጣል አድርጎ ተከታትለን መጠለያውን ከፍሎቹን ለቀን ወጣን. . ከኦመር ጋር ስንቀላለድ ከርመናልና " አሁን ከነዚህ ሁለት ቆነጃጅት ምረጥና አግብተህ ኑር ብትባል የትኛዋን ትመርጣለህ አልኩት ? ". . . ኡ. . . ኡ. . .ጀነት (ገነት) ትገባልሁ ብባል ወደ ሃገር ጦቢያ አልቀርም ተወኝ . . . " ሲል የናፈቃቸው ቤተሰቦቹ፤ የናፈቀው ቀየውና ማየት ማሽተት የሚናፍቀው የሃገሩ ምድር ናፍቆት ገለጸልኝ. . .የቆነጃጅቱን ነገር ባይጠላውም ዛሬ ይህን ማሰብ እንኳ አይፈልግም. . .ከወራት ተስፋ አስቆራጭ የጨለማ ጉዞ በኋላ ዛሬ የጨለመው በርቶ ወደ ሃገሩ ሊገባ ቀን እየቆጠረ ባለባት በዚህች ሰአት ከመሄዱ ውጭ ማሰብ አይሻም ! በመጠለያውና በካፌቴሪያ ዙሪያ ቁጭ ብለን ከችግር ጭንቀቱ ወጋወግ ወጥተን ብዙ ብዙውን የዚህ አገር አስቂኝ አጋጣሚዎቹን አጫውቶኛል. . . ይህን ማስታወሻ እየከተብኩ እንኳ አይኔ ከኮምፒውተሩ ስክሪን ከፊደላቱ ጋር እየተሯሯጠ ኦመርና ያጫወተኝ ከፊቴ ድርቅ እያለ ብቻየን ያስቀኝ ጀምሯል . . .



ሁላችንም ከግማሽ ሰአት ላላነሰ ጊዜ ቆይታ አድርገን ለመሰነባበት በድጋሜ ወደ አራስዋ እህት ጎራ ለማለት ስንሞክር ኦመር እጄን ያዝ አድርጎ በጆሮየ ሹክ አለኝ . . . ይህች መጫት ወደ ሃገር ቤት ለመግባት ፈቃደኛ አይደለችም . . . የቆንስሉ አዲሱ አምባሳደሩ መረዋን በድሪ ሳይቀር ቢማጸኗት እሻፈረን በማለቷ እናንተን እሽ ብትላችሁ እባካችሁ ተማጸኗት ነበር ያለኝ. . . ጭንቀቱ ገብቶኛል ! ይህች እህት ወደ ሃገር ቤት ትገባ ዘንድ የምንፈልግ ሁላችንም ነን . . . ግን ይህ ሊሆን እንደማይችል ከብዙ ጉትጎታ በኋላ አጫውታኛለች. . . ሃገር ላለመግባት በቂ ምክንያት እንዳላት አውቃለሁ ! የሞቀ ትዳሯን የደረሱ ልጆችዋን ለባልዋ በትናና አረብ ሃገር ተሰዳ ሰርታ ልጆችዋን ልታሳድግ ነበር ህልሟ. . .የትዳር ቀለበቱን ሽጦና አራጣ ተበድሮ የላካት ባሏንና በስስት እያለቀሱ የተለይዋትን ሶስት ልጆቿን ትታ ወደ አረብ ሃገር የመጣች በጅቡት በኩል ቀይ ባህርን ተሻግራ፤ የየመን በርሃ ቆርጣ ሳውዲ የገባችው ከአምስት ጊዜ በላይ በግዳጅ ተደፍራ ነበር. . .ያን ሁሉ መከራ ገፍታ ጅዳ ስትገባ አራት ወራት ቢፈጅባትም የወር አበባዋ ከቀረ ሶስተኛ ወሩን ደፍኗል. . . ለሷ ገና ከጅምሩ በማህጸኗ የተያዘው ጽንስ በማታውቃቸው ሰዎች አስገድዶ መድፈር የጸነሰችው በሽታዋ ብቻ አይደለም . . . እንዳትሰራ የገደባት መሆኑም እዚህ ግባ የሚሉት ችግር አይደለም. . . የተዳከመችው ነብሰጡር ልጇን በሰላም ስትገላገል ተከትሎ የመጣው አደጋ ከሰውነት ተራ አውጧታል ! አይወለድ የለም ልጅ ተወለደ ! ችግሩ ከሌላ መከራ ጋር ነበር የመጣው ! ይህም ልታሻሽለው ከተሰደደችበት የድህነት ጎጆዋን ከሚያፈራርስ መርዝ የተናነሰ አደጋ አይደለም. . .እናም ይህን መርዝ ሳትወድ በግድ ተግታዋለች ! የሃገሯን ምድር ስትለቅ ጤነኛ እንደነበረች የምትናገረው እህት በበርሃው እንግልት በተፈጸመባት ተደጋጋሚ የወሲብ ጥቃት የዚያ ቀሳፊ በሽታ ተጠቂ አድርጓታል. . . ልጇን በወለደች ማግስት በሳውዲ መንግስት በኩል ከታወቀ ያስጠቃናል ያሉ ለነብሳቸው ያስጠጓት ወገኖች የበሽታው መዘዝ አስፈርቷቸው በቆንስል መስሪያ ቤቱ ጥለዋት ሄደዋል. . .ይህ ምሬት ካንዴም ሁለቴ ልጇን አንቃ ልትገድል እንዳስሞከራት ሰምቻለሁ . . . አሁን ግን ያ ሁሉ ስሜት ባይኖርም ቤተሰቧን ልታሻሽል ልጅ ጥላ የመጣች እህት ሌላ ልጅ ይዛ ለሌላ መከራ ሃገር ቤት መግባቱን አትቀበለውም. . . ምክንያቷን ብዙዎቻችን ላንቀበለው ብንችልም ለእርሷ በቂና ከበቂም በላይ ምክያት ነው ማለት ግን ይቻላል. . . እናም በዚህ ዙሪያ ብዙ ላነጋግራት አልቻልኩም. . . ሰላምታ ሰጥተናት ወጣን. . .ኦመር ግን ያለኝን ባለማድረጌ ደስ አላለውም . . . ፊቱ ከችም ብሎ ሲመለከተኝ ምክንያቴን ጠለቅ ብየ ባላስረዳውም ሌላ ጊዜ እንደማነጋግራት አስረድቸው ልለየው ስል ሲፍነከነክ የነበረው ኦመር መልዕክቱን ባለማስተላለፌ አዝኖ እንዲህ አለኝ " ያን በሽታ አኮ አለባት . . . በሰው ሃገር ምን ያደርጋል! . . ." እያለ ሊያስረዳኝ ሞከረ ! አሁንም በሷም ሆነ በልጇ ላይ ቀሳፊው በሽታ ስለመኖሩ ማወቄንም ሆነ ስለሌላው ችግር እንዳላዋቂ ሆኘ አድበስብሸበትና ጉዳዩ አጥፋፍቸው መጠለያውም መልቀቅ ጀመርን፡፡ ቀድመውኝ



የሚራመዱት እህቶች  ስንገባ በር ላይ ወዳየናትና ታማሚዎችን ጠያቂ ወደ መሰለችን ጉብል  ሰላምታ ሲያቀርቡላት ተራመዱ. . .ሰላምታ ሲያቀርቡላት ዝምታን በመምረጥዋ ችግር ይኖርባት ይሆን ብለው ተጠግተው ለማነጋገር ሲጠጓት ሳያስቡት  አምባረቀችባቸው. . . በፍርሃት ሲሸሹ እኔና አመር ከቅርብ ርቀት ተመለከትን . . . ይህችን እህት ያለ ዛሬ አላየኋትምና ዞሬ አመርን ጠየቅኩት "እሱማ እብዷል. . .ትናንት ገና ነው የመጣው . . . ተውት አትጠጉት. . ." አለ አመር ደንግጠው ከተበራገጉት እህቶችንስ ለኔም ጭምር  . . . አጸያፊ የሚባለውን ሁሉ ስድብ ታንጎደጉደው ገብታለች . . . እኔም ሆንኩ አመር አልቀረልንም በተሸፋፈነው ፊትዋ አንጫልቃ እያየች አገላብጣ ሰደበችን . . . አስነዋሪውን ስድብ ሳይሆን የዚህችኛዋ ሌላ መከረኛ የህይወት ውጥንቅጥ ሚስጥር ሳናውቀው አሳዝኖ አስተከዞን  የቆንስሉን ግቢ ለቀን ወጣን. . .

## ሽኝት. . .

የኮሚኒቲው ካፍቴሪያ የስድስት ወር ተረጅዎች ሊሸኙ ሁሉም ነገር ተስተካክሏል . . .የኮሚኒቲው አዳራሽ እንደ ማለዳው ሁሉ በብዙ ደንበኞች  አልደመቀም . . .አዳራሹ በመከረኛው ብሄር ብሂረሰቦች ባንዴራ ደምቋል. . . ላለፉት ስድስት ወራት በቆስንሉ መጠለያ የከረሙትን ህሙማን ወገኖች ለመጨረሻ ጊዜ የምናያቸው ዛሬ ነው ! ህሙማኑና በቅርብ የሚያውቁ ሲደግፏቸው የከረሙ በጣት የሚቆጠሩት ወንድም እህቶች በቦታው ተገኝተዋል፡፡ ለወራት በማውቀው የጉስቁል ወንድሞችና ልንሸኛቸው የመጣነው ወገኖች ፊት በርቷል . . . ከችግር ለመወጣት ወርቅ እናፍስ ብለው ሮጠው መጥተው በውስጠ ደዌ በሽታ ተቀስፈው፤  ሸባ ሆነውና ተሰናክለው በዱጋፊና በምርኩዝ መመለሳቸው ለነሱም ሆነ ለኛ ዛሬ ላይ ጸጋ ነው ! በአዳራሹ የነገሰው ደስታ በብዙ አጀብ የደመቀ ባይሆንም አሞን ለከረምነው ጥቂቶች ግን ደስታው ከምንም በላይ ነው ፡፡ እናም እነምናሴና ጀኒ አዲስ አበባ ሲዎርዱ ለመጓጓዣ የሚሆናቸው ገንዘብ ለመሰብሰብ በመካከላችን ውር ውር እያሉ ገንዘብ ሲሰበስቡ እኔም እነአመርን ገንጠል አድርጌ በመውሰድ ክራሞት ደስታቸውን በመቅረጸ ድምጼ መያዝ ጀመርኩ . . . ሁሉም በአረብ ሃገር ሰርተው አባት እናት እህት ወንድም ዘመድ አዝማዶቻቸውን ከድህነት ለማውጣት ቢመጡም ያጋጠማቸው መከራና ስቃይ በመሆኑ ሮጠው በመጡበት እግራቸው ተሰናክለውና በውስጠ ደዌ በሽታ ተቀስፈውም እኒያን ወገኖቻቸውንና ሃገራቸውን ለመቀላቀል ጓጉተዋል. . . የሆነው ሁሉ እውነት አይመስላቸውም. . . እናም ከህይዎት ተሞክሯቸው ከቋጥ ከባጡ፤ከቅርብ ከሩቁ ፤በሆዳቸው ውሎ ያደረውን አወጉኝ . . . ይህ እኔ ያለሁበት የአረብ ምድር ለኔና ለቀረነው ጥቂቶች መጨረሻው በአደጋ የተከበበ ቢሆንም ቅሉ ኑሮውን ኑሩ ብለን በሰላም እየገፋን እንገኛለን. . . የስደት ህይወታችን የክራሞትም ያህልም ቢሆን የተሳካ የሚመስለው ህይዎት ውስጡን ለቄስ ነው. . . ራሳችን አግዘን ወገናችን ለመደገፍ የምናደርገው ትግል ግን አሸናፊዎች ነን ማለት አይቻልም ! ከአመታት ስኬት የተባለ ህይወት በኋላ የቋጠነው ወረት የለምና ሃገር ቤት ጠቅልሎ መግባት ሲነሳ እንኳ ያስፈራናል. . . ለሂያጅ ወንድሞች ግን ሁኔታው ከዚህ የተለየ ነው . . . በተለይም በህምመን ተቀፍድደው ባሳለፏቸው ስድስት ወራት ሌት ተቀን ህልማቸው ሃገራቸው ገብተው ቀሪ እድሜን ከወገኖቻቸው ጋር ቆሎ ቆርጥመው መግፋት ብቻ ነው ! እውነት አላቸው. . .! ለነሱ ይህ ምድር የሰቆቃ ምድር ነበር . . .ሰብዕናቸው ተረግጦና ተገፍተውበታልና ሌላ ነገር አይሹም ! ሃገር ቤት መግባትን ብቻ ነው የሚያልሙት! በዚህ ረገድ ትልቁን ስራ ለከወኑት የቆንስል መስሪያ ቤት ሃላፊና ሰራተኞች ምስጋና ይገባቸዋል. . . በመከራቸው ጥሩ ምሳሌ የሆኑን ወገኖች ስቅየት በዚህ አበቃ ማለት ባይሆንም በስደት የሚያደርጉት ትግል ዛሬ ተፈጽሟል. . . ለቀረነው ይህ ሊያስተምረን ከቻለ እሰየው ነው. . .  መልካሙን በመመኘት ሸኘናቸው !



በቀጣይ ቀናት ወደ ቆንስል መስሪያ ቤቱ መጠለያ ጎራ ብየ ነበር. . . መጠለያው ወና ሆኗል፡፡ ያችን መጫት ከመጠለያው ታዛ ስር ብቻዋን ጸሃይ እየሞቀች አገኘኋት፡፡ ልጇ ህመሙ ጸንቶበት ዘይነብ ተብላ በምትጠራ አንዲት እህት ትብብር ወደ ሃኪም ቤት ሄዶ እርዳታ እተደረገለት እንደሆነ ሰምቻለሁ. . .እናትን ስለልጇ መጠየቅ ነበረብኝና ልጅሽ የትነው ያለው ? ብየ ጠየቅኳት. . . ህመሙ ጸንቶበት ሃኪም ቤት እንደገባ ገለጸችልኝ፡፡ ይህ የማጣራበትን መንገድ አለና ብዙ አልገፋሁም. . . ሃገር የመግባት ሃሳቧን ስለመቀየር አለመቀየሯ ግን ደጋግሜ ጠየቅኳት . . . አሁን ደግሞ ጥያቄውን እንኳ መስማት አትፈልግም. . . ማድረግ የምትፈልገውን አታውቅም አልልም. . .የምትፈልገው ነገር ቢኖርም አትናገረውም. . .ብትናገረው ፋይዳ ይኖረዋል ብላ ላትገምት ትችላለች . . .ብቻ የደረሰባት ጭንቅና መከራ  ግራ ኢጋብቷታልና ሁኔታዋ እያስፈራኝ ተለየኋት፡፡ የልጁን ሁኔታ ለማጣራት የችግር አስውጋጅ ኮሚቴ አባላት



ወደ "መፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴው " ሰራተኛ ወደ ወንድም ቴዎድሮስ ቢሮ ጎራ አልኩ፡፡ ለግላጋው ወንድም እንደተለመደው በፈገግታ ሞቅ አድርጎ ተቀበለኝ . . .ስለዚህች እህትና ህጻኑ ስላለበት ሁኔታ ጠየቅኩት. . . ቴዲ ፊቱ እየተለዋወጠ ያ ህጻን በመከራ እንደመጣ በመከራ መሸኘቱን ሲገልጽልኝ ". . .እኔና መሃመድ ሸህ ነው ብቻችን የቀበርነው!" ሲል አረዳኝ ! ይህ እምቦቃቅላም ወደማይቀረው አለም ተሸኘ . . .

# ክራሞት. . .

ሁለት ወራት ተጉዠ የእኒህን ወገኖች ውሎ አዳር ሳወጋጋ በህጋዊነት በከተምን ኢትዮጵያውያን የለት ተለት ኑሮ ዙሪያ ቀልብን የሚስብ አደጋ እየተስተዋለ ይገኛል. . . በተለይም በጅዳ አለም አቀፍ ትምህርት ቤት ዙሪያ እያንዣበበ ያለው ሁኔታ አሳሳቢ ከሆነ ሰነባብቷል . .የትምህርት አሰጣጡ ከዛሬ ነገ ይሻሻላል፤ ትምህርት ቤቱ የራሱን ህንጻ ያሰራል ተብሎ በተስፋ ከ12 አመት በላይ ቢገፋም ችግሩን ፈቀቅ የሚያደርግ ጠፍቷል፡፡ በባለቤትነት የሚያስተዳ ድረው ኮሚኒቲ ዙሪያ ገብ ይሰራል የሚባለው ሽፍጥ ማህበረሰቡን አላስቀርብ ብሎ አባላቱ በሺዎች የሚቆተሩ ዜጎች በሚገኙበት ክልል አባላቱ ለአመታት ከመቶዎች ፈቀቅ ሊል አለመቻሉ ቢያነጋግርም ችግሩን የፈተሸው የለም. . . በቅርቡ የኮሚኒቲው ጠቅላላ ጉባኤው የቀረበው የፋይናንስ ሪፖርት ሙግት በማስነሳቱ ጠቅላላ ሂሳቡ በውጭ ኦዲተር እንዲመረመር ተወስኖ እየተመረመረም ይገኛል፡፡ የትምህርት ቤቱ ባለቤት በሌላ አደጋ ሲዎድቅ 1900 ልጆቻችን የምናስተምርበት ት/ቤት አስተዳደርም "ተው ባይ" ጠፍቷልና በምግባረ ብልሹነት ታዳጊዎችን ከትምህርት ገበታቸው አግዷል. . .በዚህ ረገድ ወላጆች ለሚያሰሙትን ሮሮ ሰሚ አላገኘም ! ይህ በሆነበት ማዕከል ደግሞ የተከበረውን የማስተማር ስነ ምግባር አጎደፈ ተብሎ ከትምህርት ቤቱ የተወገዘ መምህር ት/ቤቱ አጠፋ ብሎ ይፋ ካወጣው ድርጊት ጋር ተመጣጣኝ ያልሆነ ቅጣት ነዋሪውን አስቆጥቷል. . .

የዛሬ አራት ወር ገደማ አዲስ እንደመጡ በሙሉ ሃይል ሲንቀሳቀሱ ያየናቸው አምባሳደር መርዋን በድሪ ውለው ሲያድሩ በጀመሩት ፍጥነት መጓዝ አልቻሉም. . . በጀመሩት ትጋት አልገፉበትም. . . አስራ አምስት አመት ሲንከባለል የመጣ መጠነ ሰፊ ያበጠ ችግር ጠረጴዛቸውን እንደሞላው ጥርጥር የለኝም. . . እንደ አጀማመራቸው የህዝብን እንባ እየጠረጉ ሸምጠው እንዳይሄዱ የያዛቸው ምን እንደሁ ግን ከመላ ምት ባለፈ የማውቀው የለም. . .በእርግጥ ችግሩ ብዙ ቢሆንም ማህበረሰቡን በአንድነት ከሚያገኙበት መንገድ ይልቅ መንግስት የሚደግፋቸው ማህበራትን በማደራጀቱ መግፋታቸው ግን ተቀባይነታቸውን እያሳሳ እያዳከማቸውም እንደሆነ መገመት ይቻላል . . . ! ቀድሞ የተዘራው "ወሬ አቀባይ" እንደ አሸን የመፍላቱን ያህል የማህበረሰቡን ችግር ሰምተው የመንግስት ሃላፊዎች እንዲያርሙት አመከሩ አይዘክሩም ! ጥሩነቱ አዲሱ አምባሳደር  "የወሬ አቀባይዮችን" ወሬ መስማት እንጂ የተባለውን ሁሉ በግርድፉ ይቀበላሉ ተብለው ግን አይታሙም. . . እኒህኛው ቀለም የቀመሱ ናቸውና እንደ ቀድሞ አምባሳደራችን "መረጃ እንጅ ማስረጃ የለንም" የሚሉት "ወሬ አቀባዮች" ያደናግሯቸዋልም ግን አይባልም. . . ብቻ ከላይ ያየናቸውን ህሙማንን ተሹመው በመጡ ማግስት ለሃገር እንዳበቁት ሁሉ በነዋሪው ማህበራዊ ህይዎት ዙሪያና የዜጎችን መብት በማስከበር ረገድ ቢሰሩ መልካም እንደሆነ የሚመክሩ ነዋሪዎች የትየለሌ ናቸው . . . ! አምባሳደራችን የወላጆችን ጥያቄ ለመሸፋፈን በመምህራን መካከል ሳይቀር ክፍፍል የተፈጠረበትን ሂደት ይደግፋሉ ባልልም የዝሆን ጆሮ ይስጠኝ ብለው ባይገፉበት ብዙዎቻችን ደስ ይለናል. . .የሚከፉት ጥቂት ናቸውና ! ሌላው ገንዘባችን ከፍለን የምናስተምርበት ትምህርት ቤት ወላጆች ከሚከፍሉት ክፍያ ጋር ተመጣጣኝ ትምህርት የማግኘታቸውን መብት ለማስከበር የብዙሃኑን ሙሉ ድምጽ አግኝቶ የተመረጠው የወላጅ ኮሚቴ ስራውን እንዳያከናውን በአዳባባይ ተሰናክሏል. . . ምክንያቱ የኢትዮጵያን ትምህርት ሚኒስትር ፖሊሲ ካልተከተላችሁ የሚል ነው. . . ይህንን የወላጅ ኮሚቴው ባይቃወምም ደንቡን ስጡኝ ብሎ ለወራት ሲባዝን ያቀረበለት አልነበረም . . . ያም ሆኖ የውስጥ መተዳደሪያ ደንቡን ለማስጸደቅ ባሳለፍነው ወር አጋማሽ የጠራው ስብሰባ እንዲደናቀፍ ተደርጓል . . ምክንያት ? .ደንቡ የሚጸድቀው ከመምህራን ህብረት ጋር ሲጣመር ነው በሚል ነው. . . ህብረት መፍጠሩ ባይከፋም አንድ ኮሚቴ የውስጥ መተዳደሪያ ደንቡን፤ የስራ ሃላፊዎችን ድልድልና አላማውን የሚያመላክትበት መተዳደሪያ ደንብ እንዴት አይኑረው ይባላል ? በእርግጥም ግራ ያጋባል ! ለሁሉም ሃላፊዎቻችን የአብዛኛውን ድምጽ የሚያደምጡበት አቅል ይሰጣቸው ዘንድ ጸሎቱ የኔ ብቻ አይደለም. . .የብዙዎችም ጭምር ነው ! ለሁሉም በቀጣይ ሰበር ዳሰሳየ ከስደተኞች የመከራ ህይዎት አረፍ ብለን በጅዳ ዙሪያ በከተምነው ዜጎች ዙሪያ ስላለው የተደበቀ ህይወት አንዳንድ ነገሮች አንስቶ ለመዳሰስ እስክሞክር ለዛሬውን በዚህ ላብቃ . . .

ቸር ይግጠመን !